*ሀምሌ 01/2015 ዓ.ም*

**ትምህርት ሚኒስቴር/አዲስ አበባ**

***ጋዜጣዊ መግለጫ***

**የትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት ማሻሻል ሀገር አቀፍ ህዝባዊ ንቅናቄ በአራት ክልሎች ዛሬ ሀምሌ 1/2015ዓም ተጀምሯል።**

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል "ትምህርት ለትውልድ" በሚል መሪ ቃል በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው ህዝባዊ ንቅናቄ አካል የሆነ መርሃ ግብር በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ፣ በሃረሪና በጋምቤላ ክልሎች የትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች፣ የየክልሎቹ አመራሮች እና ማህበረሰቡ በተገኙበት **ሀምሌ 1 ቀን/2015ዓ.ም** አስጀምሯል፡፡

የዚህ ሀገራዊ ንቅናቄ ዋና አላማም አብዛኞቹ የሀገራችን ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች በመሆናቸውና እነዚህን ችግሮች በመንግስት አቅም ብቻ መፍታት ስለማይቻል የት/ቤት መሠረተ ልማትን ለማሻሻል የህብረተሰቡን ተሳትፎ የሚያበረታታ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ነው። የመጨረሻው ግብም ማህበረሰቡ የመማር እና የማስተማር ሂደቶችን በብቃት እንዲደግፍ ለማስቻል እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን በባሌቤትነት እንዲይዙ ለማድረግ ነው።

*የትምህርት ሚኒስትሩ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ የትምህርት ቤቶችን ችግር ከመሰረቱ ካልፈታነው በጥራት ብናስተማራቸው ለሀገራቸውና ለመላው ማህበረሰብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ልጆችን አቅም የሚያሳጣ ነው ያሉ ሲሆን ይህ በየክልሎቹ የሚካሄደው የህዝብ ንቅናቄም በትምህርት ቤቶቻችን ያሉ ችግሮችን ከአምስት አመት ባልበለጠ ጊዜ ከስሩ ለመፍታት ያለመ መሆኑም ተናግረዋል፡፡*

በኢትዮጵያ ትምህርት ስርዓት ውስጥ በርካታ ችግሮች ቢኖሩም ከዋና ዋና ችግሮች መካከል በትምህርት ቤቶች ውስጥ ምቹ የመማሪያ አካባቢ አለመኖሩ ነው። በአሁኑ ወቅት ከ86 በመቶ በላይ የሚሆኑት የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከ71% በላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊው መሠረተ ልማት የሌላቸው በመሆኑ ተማሪዎች በአስቸጋሪ የትምህርት አካባቢዎች ውስጥ እንዲማሩ ተገደዋል።

በተጨማሪም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉት ትምህርት ቤቶች ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ ተገቢ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ የቤተ ሙከራ እና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚባሉትን መሰረታዊ መገልገያዎችን አያገኙም።

በየመድረኮቹም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭና በአገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ባለሀብቶች ለት/ቤት መሠረተ ልማት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ጥሪ ተላልፏል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ጥራትን በሚመለከት የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን እንደ ሀገር የትምህርት ስርዓቱን ከመሰረቱ በማስተካከል ትውልዱ ላይ መስራት ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education